የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

መጋቢት 27 ቀን 2010 ዓም

## ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔርዊ ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ

## የጀግና ቤት አይደፈርም

የወንድ ቤት መበርበር ድፍረት ነው፣ ትዕብተኛው ወያኔ የሰው ቤት በርግዶ መግባትና መበርበር እንደሙያ ተያይዞታል፣ ዉጤቱ ደግሞ ደመ ከልብ መሆኑ እያመላከተ ነው፣ ወያኔ አገርን ከማስደፈር አልፎ ኢትዮጵያዊ ጀግናን መናቁ ያስቆጣው ፋኖ ዱር ቤቴ ብሎ የወያኔን አጋዚ አፈር ማስጋጥ ከጀመረ ዓመት እያስቆጠረ ነው፣ **የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ\ ኢሕብፓ**] ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያበስረው ጀግናው ፋኖ ደርቤ በጎጃም ልዩ ስሙ አቸፈር በሚባል ወረዳ ቤቱን ሊፈትሹና መሣሪያውን ሊነጥቁት ከመጡት ዘልዛላ የአጋአዚ ወያኔ ወታደሮች ጋር ተኩስ ገጥሞ ስምንቶቹን(8) ገድሎ የቀሩትን አቁስሎቸው በመጨረሻ በመከበቡ እጄን ለውራዳ ለወያኔ አሽከር አልሰጥም በማለት ራሱን ሠውቷል፣ የኢሕብፓ በጀግናው መሰዋት መሆን ቢያዝንም ደርቤ በፈጸመው አኩሪ ገድል ሲያወድሰው ለአርበኛው በተሰብና ወገን በሙሉ መጽናናትን ይመኛል፤

አርበኛ ደርቤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ክብር ዘላለማዊ ታሪክ ሠርቶ ከማለፉም በላይ ለወጣት ኢትዮጵያውያን ትልቅ ምሣሌ ሆኖ ይቆጠራል፣

ፋኖ ከላይ በጠቀስነው ድል ተወስኖ አልዋለም፣ የወያኔ የደም ሥር የሆነውን ከጎንደር ሱዳን የሚወስደውን አውራ መንገድ በመዝጋት ሲያጨናንቅ ዋለ፣ በመጨረሻ የአከባቢው የወያኔ የጦር አዛዥ ከሱዳን ድጋፍ ጠይቆ ለተወሰነ ሰዓት መንገዱ ተከፍቶ ነበር፣

የፋኖ ትግል ቀጣይ ስለሆነ የጀግኖቹን ውሎ ፓርቲውና አጋሩ የኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነት በምተባበር የምናቀብ መሆኑን እንገልፃለን፤

የኢትዮጵያ አንድነት በውድ ልጆቿ ደምና አጥንት ተከብሮ ይኖራል!!

# ሕያው ታሪካችን በደም አጥንታችን ይለመልማል!!

| | |
|---|---|
|  |  |
| ኢሕብፓ EPNP የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY | ኦሕንኢአ OPMEU |

EPNP.INFO

EPNP

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ

ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PA